የ2022 እ.ኤ.አ የአፍሪካ ህብረት የመምህራን ሽልማት (Africa Union Teachers Prize)
ተወዳዳሪዎች መምረጫ መስፈርት

የአፍሪካ ህብረት የሰው ሀብት ሳይንስና ቴክኖሎጂ የስራ ክፍል በህብረቱ ለሚካሄደው የመምህራን ሽልማት (Teachers Prize) ውድድር እጩ ተወዳዳሪዎችን እንድናቀርብ ጥሪ አድርጓል።

በዚህ መሰረት አመልካቾች ለውድድር ለመቅረብ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል።

i. የአፍሪካ ህብረት አባል ሀገራት ዜግነት ያላቸው መሆን
ii. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚጠይቀውን የትምህርት ደረጃ ያሟላ/ች መሆኑን እና በማስተማር ላይ ስለመሆኑ ህጋዊ ማስረጃ የሚያቀርቡ
iii. ከሁለት ተወዳዳሪዎች መካከል አንድ ወንድና አንድ ሴት ይሆናሉ
iv. እንደ መምህር የሚከተሉትን ብቃቶች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል
    - ተማሪዎችን በከፍተኛ ደረጃ ውጤታማ ለማድረግ የሚችል ጥራት ያለው የመማር ማስተማር ስራ የሚከውን/ የምትከውን፣
    - ከወቅታዊው ዕውቀት ጋር ራሱን/ራሷን በማብቃት የሚያስተምረውን/የምታስተምረውን ትምህርት በብቃት መግለጽ የሚችል/ የምትችል፣
    - አዎንታዊ ግብረ መልስና ሌሎች ስልቶችን በመጠቀም በተማሪዎች እንዲፈጠሩ የሚፈለጉትን መልካም ባህሪያት ያጎለበተ/ያጎለበተች፣
    - የተማሪዎችን የመማር ፍላጎቶች እና ችሎታን ያማከለ የክፍል ውስጥ የትምህርት አሰጣጥ ጥራትን ለማሳደግ የመማሪያ ክፍሉን በአግባቡ መምራት የቻለ/የቻለች፣
    - ማህበራዊና ባህላዊ የትምህርት ፋይዳን በሚያጎለብቱ ተግባራትና የእርስበርስ ትስስሮች ላይ ተማሪዎችንያሳተፈ/ያሳተፈች፣
    - ተማሪዎች የረጅም ጊዜ ግባቸውን ለማሳካት እንዲችሉ ተገቢነት ካላቸው ተቋማት ጋር እንዲገናኙና የተለያዩ ጠቃሚ መረጃዎችን እንዲያገኙ እገዛ የሰጠ/የሰጠች፣
    - ዕውቀትንና ክህሎትን ለማስረጽ ከሚደረገው የመማር ማስተማር መስተጋብር ባሻገር ለሰላም ግንባታ እና ሀላፊነታቸውን የሚወጡ ዜጎችን ለመፍጠር የተለያዩ እሴቶችን የሚተገብር/የምትተገብር፣
    - የጋራ መማማርን ለማበረታታት ከአቻ መምህራን ጋር አዎንታዊ ግንኙነት ያለው/ያላት፣
    - በባለድርሻ አካላትና በህብረተሰብ በኩል መልካም ስም ያለው/ያላት፣
    - በተማሪዎቹና በስራ ባልደረቦቹ በከፍተኛ ደረጃ ተመራጭ የሆነ/የሆነች